| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "የግፉ ፡ ጽዋ ፡ ሞልቶ ፡ ፈሰሰ ። " |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ሚያዝያ ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2015-002 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

## የግፉ ፡ ጽዋ ፡ ሞልቶ ፡ ፈሰሰ ።

*" ስንደዶው ፡ ርጥቡ ፥ ስሜን ፡ ጓሳው ፡ ጤሰ ፤*
*የጐበዝ ፡ መነኻው ፡ ሰዓቱ ፡ ደረሰ ! "*

---



የመንደር-ገነን ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ አረመኔዎች ፥ መልሰው ፡ በማይማቱ ፡ ሕፃናት ፡ እና ፡ ሴቶች ፣ አሮጊቶች ፡ እና ፡ ደካሞች ፣ ካህናት ፡ እና ፡ መነኰሳት ፡ ላይ ፡ የፈሪ ፡ በትራቸውን ፡ ማሳረፋቸውን ፡ ለዐምስተኛ ፡ ዓመት ፡ አጠናክረው ፡ ቀጥለዋል ። የግፍ ፡ ጸዋው ፡ ሞልቶ ፡ ፈሷል ፤ ሰውም ፡ እግዚአብሔርም ፡ እማይታገሡበት ፡ ደረጃ ፡ ደርሰዋል ።

በ1928-31 ፡ ዓ.ም. ፥ ሀገራዊው ፡ ዡግና ፡ ደጃዝማች ፡ ዘውዴ ፡ አስፋው ፡ ዳርጌ ፥ የሸዋ ፡ ዐርበኝነትን ፡ አነሣሥተው ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በማስፋፋት ፡ ፋሺስትን ፡ በሚዋጉበት ፡ ዘመን ፥ ጥቂት ፡ ለፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ ያደሩ ፡ ባላባቶች ፡ ሕዝቡን ፡ ባርበኞች ፡ ላይ ፡ እያስነሡ ፡ በባንዳነትም ፡ አስታጥቀው ፡ እያዘመቱባቸው ፡ ተቸግረው ፡ ነበር ። ካርበኞችም ፡ ወገን ፡ በቍጣ ፦ *"ባንዳዎች ፡ ናቸው ፥ እንበላቸው !"* እያሉ ፡ ለመዋጋት ፡ ሲጋበዙ ፥ አባ ፡ በላይ ፡ ዘውዴ ፥ የነገን ፡ ዐብሮ ፡ መኖር ፡ በማሰብ ፦ *"ተዉ ፥ አትግደሏቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ክፉኛ ፡ ሳቷቸው ፡ ..."* ፥ በማለት ፥ ብዙም ፡ ሰው ፡ ሳይሞት ፥ ተኵስ ፡ የሰማውም ፡ ባንዳ ፡ ሳይዋጋ ፡ ወዲያው ፡ እየነቀለ ፥ ከዚያም ፡ ዐልፎ ፡ ካርበኝነቱ ፡ ሚና ፡ እየተቀላቀለ ፡ ፋሺስትን ፡ መልሶ ፡ እንዲወጋ ፡ አድርገውታል ።

ደጋግ ፡ አባቶቻችንና ፡ እናቶቻችን ፡ እጅግ ፡ ጥበበኞች ፡ ነበሩ ። ዛሬ ፡ የገጠሙን ፡ ችግሮች ፡ ሳይገጥሟቸው ፡ ቀርተው ፡ አይደለም ፤ ገጥመዋቸው ፡ በጥበብ ፡ እና ፡ በቈራጥነት ፡ ኹሉንም ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ፈትተዋቸው ፥ ነጻነትን ፡ ከእነርስታቸው ፡ አውርሰውን ፡ ወደ ፡ ዘላለማዊው ፡ ሕይወት ፡ ተሸጋግረዋል ። ተመልሰው ፡ አይመጡልንም ፤ እኛው ፡ እንወቅበት !

ትላንት ፥ ምልከኞች ፡ ("ኢምፔሪያሊስቶች") ፡ ጦራቸውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ሲያዘምቱ ፥ ሕዝቧን ፡ ከምድር ፡ ገጽ ፡ አጥፍተው ፥ እነሱ ፡ ሀገራችን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሊቀራመቱ ፡ እና ፡ ተነግሮ ፡ በማያበቃ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቷ ፡ ሊቀማጠሉ ፡ ነበር ። ዐርበኞች ፡ አደብ ፡ አስገዝተው ፡ አባረዋቸዋል ። ዛሬ ፡ ደግሞ ፥ ተሐድሶ-ምልከኞች ፡ እንደ ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ ያሉ ፡ መንደር-ገነንን ፡ እሥልጣኑ ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ ሰቅለው ፡ በሽልማትም ፡ አንቈጥቍጠው ፦ *"ፈንታውን ፥ የኢትዮጵያን ፡ ጸጋዎች ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ያስረክበናል"* ፡ ብለው ፡ ጧት ፡ ማታ ፡ በዙሪያው ፡ ጕድጕድ ፡ እያሉ ፥ ዐጀቡን ፡ ሲያደምቁለት ፡ ይታያሉ ። 200 ፡ ቢልዮን ፡ ዶላር ፡ ወይም ፡ በዋጋቢሱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ምንዛሪ ፥ 15 ፡ ትሪልዮን ፡ ብር ፡ የሚገመት ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2015 ፡ ዓ.ም. ።

የመንግሥት ፡ እና ፡ የሕዝብ ፡ ሀብት ፡ እና ፡ ንብረት ፥ ከ***ኢትዮ-ቴሌኮም*** ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ***ኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድ*** ፥ ከ***ኢትዮጵያ ፡ መብራት ፡ ኀይል*** ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ***የኢትዮጵያ ፡ ውሃ ፡ ባለሥልጣን*** ፥ ከወርቅ ፡ ማዕድናት ፡ እስከ ፡ ጋዝ ፡ እና ፡ ነዳጅ ፡ ክምችቶች ፣ ምርጥ ፡ ምርጥ ፡ የዕርሻ ፡ መሬቶች ፡ እና ፡ የከተማ ፡ ቦታዎች ፣ ወዘተርፈ ፡ ... ፥ ለውጭ ፡ መንግሥታት ፡ እና ፡ ድርጅቶች ፡ በቀብድ ፡ ተይዘዋል ። ያዲስ ፡ አበባ ፡ ውድ ፡ ውድ ፡ ቦታዎች ፡ ለ"ሄጅ ፡ ፋንዶች" ፡ ተቸብችበው ፡ ዐልቀዋል ፤ የቀሩ ፡ ቢኖሩ ፥ እነሱንም ፡ አንሸጥም ፡ ብለው ፡ ዐኙ ፡ ያሉትን ፡ "ባለሊሶች" ፡ በመቶ ፡ ሚልዮን ፡ የሚቈጠር ፡ ብር ፡ እያቀኈለጨለጩላቸው ፥ "ባለሊሶቹም" ፦ *"አዳኑኝ ፡ ሳታባርረኝ ፡ በፊት ፡ ..."* ፡ እያሉ ፥ በጥድፊያ ፡ እያስረከቡ ፥ ሚልዮን ፡ ብራቸውንም ፡ በዶላር ፡ እየመነዘሩ ፡ (እያሚሸሹ) ፡ በሰላም ፡ ወደሚኖርበት ፡ ምዕራቡ ፡ ዓለም ፡ ከእነቤተሰባቸው ፡ ይሸጋገራሉ ። የቋጠሯትን ፡ ጥሪታቸውንስ ፡ የት ፡ ያድርጓት ፡፡ መልሰው ፡ ርስታቸውን ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ ለገዟቸው ፡ ቱጃሮች ፡ እያስረከቡ ፦ *"ምቴን ፡ በባዕድ ፡ አገር ፡ አድርግልኝ"* ፡ እያሉ ፡ የቀረቻቸውን ፡ ዕድሜ ፡ በስደት ፡ ዓለም ፡ ከማጣጣም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ማማረጫ ፡ የለም ።

ጨዋታው ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ደርቶ ፡ ነበር ፥ ***"የዐማራ ፡ ፋኖ ፡ እና ፡ ልዩ ፡ ኀይል"*** ፡ ድንገት ፡ አፈረሱት ፡ እንጂ ፡ ... ።

ነገሩ ፡ ኹሉ ፡ ገና ፡ ከመነሻው ፡ የማያዛልቅ ፡ ነበር ። ***"የዐይጠ ፡ መጎጥ ፡ ፖለቲካ"*** ፡ የምንለው ፡ ዐይነት ፡ ነው ። ዐይጠ ፡ መጎጥ ፥ ገብቶ ፡ መብላቱን ፡ እንጂ ፥ በልቶ ፡ መውጣቱን ፡ አያስብም ። ***"ወጥመድ"*** ፡ የሚባለው ፡ ነገር ፡ በሆዱ ፡ ለተቃኘው ፡ ሐሳቡ ፡ ባዳ ፡ ነው ። እ"ብጽልጽግና ፡ ፓርቲ" ፡ ውስጥ ፡ ዘው ፡ ያሉት ፡ ሡኩቴዎችም ፥ ገብተው ፡ መብላታቸውን ፡ እንጂ ፥ በልተው ፡ መውጣታቸውን ፡ አያስቡትም ። ሕጋዊ ፡ መንግሥት ፡ በሌለበት ፥ ጠፊውን ፡ መንደር-ገነን ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድን ፡ ብቻ ፡ ተማምነው ፡ ቢልዮን ፡ ዶላራቸውን ፡ እያፈሰሱ ፡ የሕዝብን ፡ ርስት ፡ እና ፡ የሀገር ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሀብት ፡ አላግባብ ፡ የሚቀራመቱት ፡ ነጣቂዎችም ፥ ከስግብግብነታቸው ፡ የተነሣ ፥ ለባለቤትነታቸው ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ሕጋዊ ፡ ዋስትና ፡ እንደማይኖራቸው ፥ ባዷቸውንም ፡ እንደሚቀሩ ፡ ማሰብ ፡ ተስኗቸዋል ።

ርግጥ ፡ ነው ፦ *"ጨዋታውን ፡ ሊያፈርስ ፡ የሚችለው ፡ ዐማራው ፡ ብቻ ፡ ነው"* ፡ ብለው ፡ ስለሚያምኑ ፥ የዐማራውን ፡ "የዠርባ ፡ ዐጥንት" ፡ ለመስበር ፡ እንደ ፡ ፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ ኹሉ ፡ ብዙ ፡ ሞክረዋል ። ይኸው ፡ ስግብግብነታቸው ፡ ዐማራ ፡ የመሳ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የግብር ፡ ስሙ ፣ የሀገራዊነቱ ፡ መገለጫው ፡ መኾኑን ፡ ከመቀበል ፡ አኹንም ፡ ስለሚከለክላቸው ፦ *" ነጥለን ፡ እንመታዋለን ! "* ፡ እያሉ ፥ በ"ክልል" ፡ አግደው ፥ "ወያኔ" ፡ እና ፡ "ኦነግ" ፡ የተባሉ ፡ ተሐድሶ-ባንዳዎቻቸውን ፡ ጦር ፡ አስታጥቀው ፡ ደጋግመው ፡ ለቀውበታል ። ነገር ፡ ግን ፥ በእየአካባቢው ፥ "ጉራጌውም" ፣ "ሶማሌውም" ፣ "ገምቤላውም" ፣ "ወላይታውም" ፣ "ዐፈሩም" ፣ "ኦሮሞውም" ፣ "ትግሬውም" ፣ ... ፥ ከጥቂት ፡ ኳደሬዎች ፡ እና ፡ ባንዳዎች ፡ በቀር ፥ ኹሉም ፡ ኅብረተሰብ ፡ ዐማራ ፡ ኾኖ ፡ ተገኝቷል ፤ አልተባበራቸውም ።

ሞኝነቱ ፡ ብልጠት ፡ የሚመስለው ፡ መንደር-ገነን ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ ግን ፥ "ፍየሏን ፡ እንደ ፡ በግ" ፦ *"ለጉራጌ ፡ ማኅበረሰብ ፡ ክልል ፡ አይጠቅመውም ፡ ..."* ፡ እያለ ፥ በሀገራዊነቱ ፡ ፍጹም ፡ ዐማራ ፣ ፍጹም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ባለቤት ፡ የኾነውን ፡ የጉራጌ ፡ ማኅበረሰብ ፡ በእልክ ፡ ወደ ፡ "ክልል" ፡ መሥመር ፡ እንዲገባለት ፡ ደጋግሞ ፡ እየተነኰሰ ፡ ቢገፋፋውም ፡ ቅሉ ፥ ከንቱ ፡ ድካም ፡ ኾኖ ፡ ቀርቷል ፤ የተሞኘለት ፡ አልተገኘም ።

መሳ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፦ *"እንቢ ! ውንብድና ፡ በቃኝ !"* ፡ ብሎ ፥ ላይመለስ ፡ ቈርጦ ፡ ተነሥቷል ። ለትኽክለኛው ፡ ሀገራዊ ፡ ዐላማ ፡ ለሚያታግለው ፡ ኀይል ፡ ሊሰለፍ ፡ እና ፡ የሚጠየቀውን ፡ ዋጋ ፡ ኹሉ ፡ ሳያመነታ ፡ ሊከፍል ፡ ዝግጁ ፡ ኾኗል ። ኢትዮጵያ ፡ ርስቱ ፡ ናት ፥ ርሱም ፡ አንድያው ፡ ባለቤቷ ፡ ነው ። ይህን ፡ ሀገራዊ ፡ እግዚእናውን ፡ ዳግም ፡ ያስከብራል ። ሊያሳስቱት ፡ የሚሞክሩ ፡ ያሉበትን ፡ ያኽል ፥ ሊመሩትም ፡ የሚወዱ ፡ ዐሥር ፡ ዕጥፉን ፡ ስላሉለት ፥ ከንግዲህ ፡ መንገዱ ፡ አስቸጋሪ ፡ አይኾንበትም ።

የአህጉራዊው ፡ ግንኙነት ፡ ኹኔታም ፥ የጠላቶቹን ፡ ዐቅም ፡ እጅጉን ፡ ወስኖለታል ። ጠላት ፥ የሚውለው ፡ እያንዳንዱ ፡ ደባ ፥ አደገኛ ፡ ጦሱንና ፡ መዘዙን ፡ ወዲያው ፡ ባልተጠበቀ ፡ መንገድ ፡ እየከሠተበት ፡ ተቸግሯል ። ትላንት ፡ የብሪታንያ ፡ መንግሥት ፥ "ለታላቋ ፡ ሶማልያ" ፡ እውን ፡ መኾን ፡ 14 ፡ ሚልዮን ፡ ፓውንድ ፡ (አንድ ፡ ቢልዮን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር) ፡ አፍስሶ ፡ የገነባው ፡ "የሶማሌ ፡ ክልል ፡ ልዩ ፡ ኀይል" ፥ እንሆ ፡ ዛሬ ፡ "የዐማራ ፡ ክልል ፡ ልዩ ፡ ኀይል"ን ፡ ወልዶ ፥ ኹኔታውን ፡ ፈጽሞ ፡ ገልብጦት ፥ ለዘመናት ፡


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2015 ፡ ዓ.ም. ።

ሲውጠነጠን ፡ የኖረውን ፡ ኢትዮጵያን ፡ የማፈራረስ ፡ ሤራ ፡ አርክሶታል ።

በዚህም ፡ አላበቃ ፤ ከሑመራ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ማጂ ፡ የሚዘረጋውን ፡ ወርቃም ፡ ምድር ፥ ኢትዮጵያ ፡ በሥልጣን ፡ ጦርነት ፡ ስትተራመስ ፥ ሱዳን ፡ እና ፡ ደቡብ ፡ ሱዳን ፡ እንዲቀራመቱትና ፡ ነጣቂዎች ፡ አንዳች ፡ ጠያቂ ፡ ሳይኖርባቸው ፡ እንደ ፡ ልባቸው ፡ እንዲዝቁት ፡ ሲታሰብ ፥ እንሆ ፡ ሰሞኑን ፡ በሱዳን ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ አመጣባቸው ። ከዳርፉር ፡ እስከ ፡ ቀይ ፡ ባሕር ፡ ግዛቷ ፥ ሱዳን ፡ በውስጧ ፡ ያመቀችው ፡ የተዳፈነ ፡ የመበታተን ፡ እሳት ፡ እንዳይቀጣጠል ፡ ያሠጋል ። ያፍሪቃ ፡ ቀንድ ፥ ከሱዳን ፡ እስከ ፡ ኬንያ ፣ ከደቡብ ፡ ሱዳን ፡ እስከ ፡ ሶማልያ ፥ በሥልጣን ፡ ጦርነት ፡ ታምሷል ፤ አካባቢው ፡ ፈጽሞ ፡ ተዘናብሏል ። ማእከላውያን ፡ መንግሥታቱ ፡ ተዳክመው ፡ የመበታተኑ ፡ አደጋ ፡ ሲያይል ፥ "every crisis is an opportunity" ፡ በሚለው ፡ የነጋዴዎች ፡ መርሕ ፥ የተሐድሶ-ምልክዮሽ ፡ ኀይሎች ፡ ያፍሪቃ ፡ ቀንድን ፡ ለብዝበዛቸው ፡ በሚያመች ፡ መንገድ ፡ በተዳብሎ ፡ (በ confederation) ፡ መልክ ፡ ዳግም ፡ ለማዋቀር ፡ አጋጣሚ ፡ የተፈጠረላቸው ፡ ሊመስላቸው ፡ ይችላል ። ለመፈጸም ፡ ግን ፡ ፋታም ፡ አያገኙ ።

አካባቢው ፡ 240 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች ፡ አሉት ፤ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ በሕገ ፡ ወጥ ፡ መንገድ ፡ በባሕርና ፡ በየብስ ፡ ከሚፈልሱት ፡ መጤዎች ፡ ውስጥ ፡ 1/10 ኛው ፡ መነሻቸው ፡ የአፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ ነው ። ከአፍሪቃ ፡ እና ፡ ከእስያ ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ የሚፈልሱት ፡ ስደተኞች ፡ መጠን ፡ በ 2015 ፡ ዓ.ም ፡ ከዓምናው ፡ በ 3 ፡ ዕጥፍ ፡ አድጓል ። የኡክራይና ፡ እና ፡ የታይዋን ፡ ጕዳይ ፡ እንቅልፍ ፡ በነሣበት ፡ በዚህ ፡ ሰዓት ፥ የአፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ ኹኔታ ፡ መባባስ ፡ ቢቀጥል ፡ ደግሞ ፥ እነኢጣሊያ ፡ እና ፡ እነግሪክ ፣ እነሁንጋሪያ ፡ እና ፡ እነፍራንስ ፥ በጠቅላላው ፡ የአውሮፓ ፡ ኅብረት ፡ ሀገሮች ፡ ሊያስተናግዱ ፡ እማይችሉት ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ይደረስና ፥ ስብራቱ ፡ ዓለም ፡ ዐቀፍ ፡ ይኾናል ፤ ጕዳቱም ፡ በእነርሱ ፡ ይብሳል ።

በአፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ የውስጥ ፡ ጕዳይ ፡ እጄን ፡ ልክተት ፡ ማለት ፡ ለመቃጠል ፡ ነውና ፥ ኹሉም ፡ በደጃፉ ፡ ያለውን ፡ ጕድፍ ፡ ቢያጸዳ ፣ አትክልቱንም ፡ ቢኰተኵት ፡ ይሻለዋል ።

ሱዳንም ፡ ችግሯን ፡ ራሷ ፡ ትፍታ ፥ በጎረቤት ፡ ሀገር ፡ የውስጥ ፡ ጕዳይም ፡ አትግባ ፥ የተሐድሶ-ምልከኞችም ፡ መሣሪያ ፡ አትኹን ።

ኢትዮጵያም ፡ የራሷን ፡ ችግር ፡ ራሷ ፡ ትፍታ ፥ በተሐድሶ-ምልከኞች ፡ ላይ ፡ በሯን ፡ ትዝጋ ፥ ወኪሎቻቸውንም ፡ ከሥልጣኗ ፡ ሰገነት ፡ ታውርድ ። በዚህ ፡ ረገድ ፥ የኢትዮጵያ ፡ የመከላከያ ፡ ሰራዊት ፡ እና ፡ የጸጥታ ፡ ሰራዊት ፡ አባላት ፡ የተለየ ፡ ኀላፊነት ፡ አለባቸው ። የሀገርን ፡ ነጻነትና ፡ የሕዝብን ፡ ሰላም ፡ ለመጠበቅ ፡ የቆሙ ፡ ኀይሎች ፡ እንደ ፡ መኾናቸው ፡ መጠን ፥ ሚናቸውን ፡ ለይተው ፥ ለሀገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ እና ፡ ከሕዝቧ ፡ ጐን ፡ ይሰለፉ ።

**የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ (ኢ.ሀ.ሥ.አ.)** ፥ ለረዥም ፡ ዘመን ፡ ሲመክርበት ፡ የነበረውን ፡ ***"ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ሀገራዊ ፡ ቅያስ"*** ፥ እንሆ ፥ መስከረም ፡ 16 ፡ ቀን ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ በሙሉ ፡ ድምፅ ፡ አጽድቆት ፥ ሚያዝያ ፡ 21 ፡ ቀን ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አስተያየት ፡ ይፋ ፡ ማውጣቱን ፡ አስታውቋል ። **ሰነዱን ፡ መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ መክሮበት ፡ ሲስማማበት ፥ በርሱ ፡ መሠረት ፡ በአንድነት ፡ ለትግል ፡ በመሰማራት ፡ እና ፡ ጠላቶቹን ፡ በማሳፈር ፥ ባጪር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሀገራዊ ፡ እግዚእናውን ፡ ሊያስከብርና ፥ ዐዲሱን ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ሠርቶ ፥ ሥልጡንሕዝባዊት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ዳግም ፡ ሊመሠርት ፡ ይችላል ።**

ይህን ፡ ደኀኛ ፡ ዜና ፡ የሰማ ፡ ኹሉ ፥ በተለይ ፡ የማወራኛ ፡ ድርጅት ፥ ላልሰማ ፡ ያሰማ ። በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፥ በእየከተማው ፣ በእየመንደሩ ፣ በእየቀበሌው ፡ በእየጭቃው ፥ ኢትዮጵያዊ ፡ ኹሉ ፡ መልክቱ ፡ ይድረሰው ፤ በሰፊው ፡ ይምከርበትና ፡ ሀገራዊ ፡ መፍትሔውን ፡ ያግኝ ፥ ኢትዮጵያንም ፡ በአንድነት ፡ ይታደግ ። ቸር ፡ ያሰማን ❖

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!

ኢ.ሀ.ሥ.አ

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2015 ፡ ዓ.ም. ።